## ኢትዮጵያ፡ ለጋሾች የእርዳታ ገንዘብ ከታቀደለት ዓላማ ውጭ ስለመዋሉ ማጣራት አለባቸው

### ብሔራዊ ፓርላማዎችና የቁጥጥር ተቋማት ተጠያቂነት እነዱኖር ግፊት ማድረግ አለባቸው

(**ኒው ዮርክ ታህሳስ 7 ቀን 2003 ዓ.ም**) የኢትዮጵያ መንግስት እርዳታን አፈናን ለማራመድ ይጠቀምበታል በማለት በሚቀርቡ ክሶች ላይ ለጋሾች ነፃ የሆነ ምርመራ ማድረግ አለባቸው ሲል ሂዩማን ራይትስ ዎች ዛሬ 26 አባላት ላሉት የልማት አጋሮች ቡድን በላከው ደብዳቤ አስታወቀ።

ሁለት መቶ ከሚደርሱ ሰዎች ጋር ቃለ ምልልስ በማድረግ ባሰባሰበው መረጃ መነሻነት በጥቅምት ወር 2003 ባወጣው ሪፖርት የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት የተቃዋሚ ደጋፊዎች በሚኗቸው ወገኖች ላይ እንዴት አድልኦ እንደሚፈጽሙ ገልጾ ነበር። ሪፖርቱ ለገዢው ፓርቲ ድጋፍ መስጠትን መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት እንደሚያስፈልግ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ መንግስት በታላላቅ ዓለማቀፍ ለጋሾች ድጋፍ ከሚደረግላቸው ፕሮግራሞች የሚያገኘውን ጨምሮ የመንግስትን ሃብት የፖለቲካተቃዋሚዎችን ለማፈን እንደሚጠቀምበት ያሳየ ነው።

የሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ዳይሬክተር የሆኑት ሮና ፔሊጋል እንዳሉት "ለጋሾች የኢትዮጵያ መንግስት እርዳታን ላልታቀደለት ዓላማ ማዋሉን አስመልክቶ ነጻ የሆነ ምርመራና ማጣራት ማድረግ አለባቸው። ለጋሽ ሀገሮች የሚሰጡት እርዳታ ሰብአዊ መብቶችን ለመጣስ እየዋለ እንዳልሆነ በየሀገሮቻቸው ላሉ ግብር ከፋዮችና ለእርዳታ ፈላጊ ኢትዮጵያውያን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው።"

ሂዩማን ራይትስ ዎች "ልማት ያለነፃነት፡ እርዳታ ኢትዮጵያ ውስጥ አፈናን እንዴት እንደሚደግፍ" በሚል ርዕስ ላወጣው ባለ 105 ገጽ ሪፖርት ምላሽ የልማት አጋሮች ቡድን (ዳግ) ጥቅምት 11 ቀን 2003 ዓ.ም የጋራ መግለጫ አውጥቷል። ቡድኑ "ሂዩማን ራይትስ ዎች የልማት እርዳታን ላልታቀደለት ዓላማ የማዋል ሥራ በስፋትና በተቀነባበረ ሁኔታ የሚካሄድ ነው በማለት የደረሰበትን መደምደሚያ የምንስማማበት አይደለም፤ የእኛ ጥናት ችግሩ በስፋት የሚታይና በተቀነባበረ ሁኔታ የሚፈጸም ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላገኘም።" በማለት ገልጾአል።

ሂዩማን ራይትስ ዎች የልማት አጋሮች ቡድኑ በሪፖርቱ ውስጥ የተካተቱት መደምደሚያዎች ላይ ላለመስማማት ያቀረበው ማስረጃ በቂ አይደለም በማለት የገለጸ ሲሆን ለጋሾች በችግሩ ላይ ነፃ ምርመራና ማጣራት አልጀመሩም፤ በመግለጫቸው የተጠቀሰው ጥናትም አራት የእርዳታ ፕሮግራሞች ያሏቸውን የአፈጻጸም መከታተያ ስልቶች ለመፈተሽ እ.ኤ.አ በ2010 መጀመሪያ ላይ በቢሮ ውስጥ የተደረገ ትንተናና "የዳሰሳ" ጥናት ከመሆኑም በላይ የመከታተያ ስልቶቹ በተግባር እንዴት እንደሚሰሩ ለማወቅ የመስክ ጥናት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ራሱ ጥናቱ የሚጠቁም መሆኑን አስታውቋል።

"ትክክለኛ ምርመራና ማጣራት ሳያካሂዱ ለጋሾች የችግሩን ስፋት ሊያውቁ አይችሉም" የሚሉት ፔሊጋል "የየሀገሮቹ ፓርላማዎች ተአማኒነት ያለው ምርመራና ኢትዮጵያን የሚመለከቱ የእርዳታ ፖሊሲዎች ላይ ወቅታዊና ጥልቅ ፍተሻ እንዲካሄድ መጠየቅ አለባቸው።" ብለዋል።

ሂዩማን ራይትስ ዎች በሪፖርቱ ሁሉም የልማት ፕሮግራሞች እንዲቋረጡ አልጠየቀም።ነገር ግን አንዳንድ ከመልካም አስተዳደር ጋር የተያያዙ ፕሮግራሞች የኢትዮጵያ መንግስት አፋኝ የሆኑ ሕጎች መሻርን የመሳሰሉ ቁልፍ የሆኑ መስፈርቶችን እስኪያሟላ ድረስ መቋረጥ እንዳለባቸው ለጋሾችን አጥብቆ ጠይቋል። መቋረጥ ከሚገባቸው መካከል ሀገር በቀል የተጠያቂነት ሥርዓትን ለማስፈን በማሰብ እንደፓርላማ ላሉ ተቋማት የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ የሚደረግበት የዲሞክራሲ ተቋማት ፕሮግራም/ዲፕ/ አንዱ ነው። ተጠያቂነትን ለማስፈን እጅግ አስፈላጊ የሆኑት ነፃ የሆኑ ተቋማት፣መገናኛ ብዙሃንና ሲቪል ማህበረሰብ በሌሉበት ሁኔታ ለጋሾች ለዚህ ፕሮግራም ድጋፍ ማድረጋቸውን መቀጠል የለባቸውም። በማለት ሂዩማን ራይትስ ዎች ገልጾአል።

"የሰብአዊ መብቶች አያያዙ እየከፋ በሄደ ቁጥር ለኢትዮጵያ መንግስት የሚሰጠው እርዳታ ጨምሯል። የገንዘብ ድጋፉን ያለበቂ የመከታተያ ስልት በመጨመር ለጋሾች የራሳቸውን የሰብአዊ መብቶችና የመልካም አስተዳደር መርሆች እየተጻረሩ ነው።" ብለዋል ፔሊጋል።

*ደጋፊ መረጃዎች*

አወዛጋቢና ደም አፋሳሽ ከነበረው የ 1997 ምርጫ በኋላ በኢትዮጵያ ያለው የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ አሳሳቢና ቀጣይ የሆነ ማሽቆልቆል አሳይቷል። ምርጫውን ተከትሎ በተቀሰቀሰ ተቃውሞ ሳቢያ ቢያንስ 200 ሰዎች ሲገደሉ ከ30000 በላይ ሰዎች ለእስር ተዳርገዋል።ከዚያ ወዲህ ባለው ጊዜ የኢትዮጵያ መንግስት የፖለቲካ ምህዳሩን ቀስ በቀስ ዘግቶአል፣ነፃ ጋዜጠኞችን አሳዶአል፣ የሲቪል ማኅበረሰብ መሪዎችን ድምጽ እንዲታፈን ወይም ለስደት እንዲዳረጉ አድርጓል፤ እንዲሁም የመደራጀትና ሐሳብን በነፃ የመግለጽ መብቶች ጥሷል።

እ.ኤ.አ በ2009 የጸደቀው የሲቪል ማኅበራት ሕግ ከ 10 በመቶ በላይ ገቢያቸውን ከውጭ ምንጮች የሚያገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሰብአዊ መብቶች፣ከመልካም አስተዳደር እና ከግጭት አፈታት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ሥራዎችን እንዳይሰሩ ከልክሏል። ሕጉ አብዛኞቹ ነፃ የሰብአዊ መብቶች ድርጅቶች እንዲዘጉ ወይም ሥራዎቻቸውን በከፍተኛ መጠን እንዲቀንሱ ሌሎቹም የሚሰሩባቸውን ጉዳዮች እንዲቀይሩ አስገድዷል።

የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ዓለማቀፍ መመዘኛዎችን ያላሟላ በማለት በገለጹትና በግንቦት ወር 2002 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ ገዢው ፓርቲ በፓርላማ ከሚገኙ መቀመጫዎች ውስጥ 99.6 በመቶውን አሸንፏል። የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን እ.ኤ.አ ኖቬምበር 8 ቀን 2010 ባወጣው የመጨረሻ ሪፖርት ገዢው ፓርቲ በምርጫ ዘመቻ ወቅት የመንግስትን ሃብት ያለአግባብ ይጠቀም እንደነበረ በመግለጽ ተችቶታል።

በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ እየከፋ በሄደ ቁጥር ለጋሾች ዕርዳታቸውን ጨምረዋል። እ.ኤ.አ ከ 2004-2008 ባሉት ዓመታት ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ዓለማቀፍ የልማት ዕርዳታ በእጥፍ በማደግ በዓመት ወደ 3.3 ቢሊየን ዶላር ደርሷል። ይህም ኢትዮጵያን በአፍሪካ ውስጥ ከፍተኛ እርዳታ ተቀባይ ከሆኑ ሀገሮች አንዷ አድርጓታል።

**ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ተጨማሪ የሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርቶችን ለማግኘት የሚከተለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ**

http://www.hrw.org/en/news/2010/10/18/ethiopia-donor-aid-supports-repression

**ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ተጨማሪ የሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርቶችን ለማግኘት የሚከተለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ**

http://www.hrw.org/africa/ethiopia

**ለተጨማሪ መረጃ፡-**

ዋሽንግተን ዲሲ፡ ሌስሊ ሌፍኮ (እንግሊዝኛ) +1-240-486-7259 (ሞባይል)
ለንደን፡ ቶም ፖርቲየስ (እንግሊዝኛ) +44-207-713-2766 ወይም +44-79-8398-4982 (ሞባይል)
ናይሮቢ፡ ቤን ራውለንስ (እንግሊዝኛ፣ ስዋሂሊ) +254-725-369-652 (ሞባይል)
ብራሰልስ፡ ሎተ ሌሽት (እንግሊዝኛ፣ፈረንረሳይኛ፣ጀርመንኛ፣ዴኒሽ) +32-2-737-1482 ወይም +32-47-568-1708 (ሞባይል)